# በኢሕአፓ ላይ የሚካሄደው መጠነ-ሰፊ ወከባ ትግላችንን አያስቆመውም!

ድርጅታችን ኢሕአፓ ከመላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ጋር በመሆን ለእኩልነት፣ ለፍትኅና ለዴሞክራሲ ሲታገል ከግማሽ ምዕተ-ዓመት በላይ አስቆጥሯል። ለዘመናት በሕዝባችን ላይ ሰፍኖ የነበረውን ባላባታዊ ሥርዓት፣ ለአሥራ ሰባት ዓመታት አገሪቱን ሲያምሳት የኖረውን የወታደራዊ አምባገነን መንግሥት እንዲሁም የህወሓትን ዘረኛ አገዛዝ ለማስወገድ የተለያዩ ሕዝባዊ አመፆችን በከተማ ውስጥ በመምራት እንዲሁም በገጠሪቱ ኢትዮጵያ መሣሪያ አንስቶ ሲታገል የኖረ ድርጅት ነው ኢሕአፓ። በዚህም የትግል ዘመኑ ከፍተኛውን መስዋዕትነትን በመክፈል ታሪክ ሲዘክራቸው የሚኖረውን ሥርነቀል ለውጦች በአገራችን ውስጥ ዕውን እንዲሆኑ የድርሻውን አበርክቷል። ዛሬም ኢትዮጵያውያን በሉዓላዊ አገራቸው ላይ የማይገሰስ ሥልጣናቸውን አስከብረው እኩልነት፣ ፍትኅና ዴሞክራሲን እስከሚቀዳጁ ድረስ ትግሉን እንደሚቀጥል በማመን ሙሉ ድጋፋችንን ለድርጅታችን እንሰጣለን።

ዛሬ ኢትዮጵያ በቀድሞ አገዛዞች ሥር ከነበረችበት በከፋ ሁኔታዎች ውስጥ ትገኛለች። በማኅበራዊ ዘርፍ ዜጎች ሰላምና መረጋጋትን አጥተው፣ ከቄያቸው የሚፈናቀሉባት፣ በአደባባይ የሚታፈኑባት፣ የሚታገቱባት ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴአቸው የተገደበባት፣ ቤተ-ዕምነቶቻቸው የሚፈርሱባትና በከባድ መሣሪያዎች የሚደበደቡባት፣ ረሃብና ዕርዛትን ኑሮዬ ብለው እንዲቀብሉ የተጻረጉባት አገር ሆናለች።

በኤኮኖሚው ዘርፍም ቢሆን የአገሪቷ ገንዘብ የመግዛት አቅሙ በየቀኑ እያሽቆለቆለ የሚገኝበት ጊዜ ነው። በአንዳንድ ክልሎች ደሞዝ ያልተከፈላቸው ሠራተኞች ጥያቄያቸውን በሰላማዊ መንገድ በአደባባይ ይዘው ስለወጡ የተሰጣቸው ምላሽ ድብደባ፣ እሥራትና ሌላም ሌላም ሁኗል። የመንግሥት ሠራተኞች እያስራብ ባለ ኤኮኖሚ ውስጥ ነው አገራችን በልጽጋለች፣ ኤኮኖሚዋ አድጓል እየተባለ ሊያሳምኑን የሚሞክሩት። በየደረጃው ያሉ የመንግሥት ባለሥልጣኖች በሙስና የተዘፈቁ መሆናቸው ግልጽ ሆኖ ሳለ ይህንን እውነታ የብልጽናው መንግሥት እያየና እያወቀ እንዳላወቀ ለመምሰል ሲሞክርም እየተስተዋለ ነው።

አገራዊ ደህንነትን በተመለከተ፣ አገራችን በቅርብ ጊዜ ታሪኳ አይታ በማታውቀው ደረጃ የአገሪቱን ሁለት ሦስተኛውን ሕዝብ ባቀፉት የአማራና የኦሮሚያ ክልሎች አስከፊ ጦርነቶች እየተካሄዱ ነው። በሌሎች ክልሎችም ሰላምና መረጋጋት ሙሉ በሙሉ ሰፍኖ አይታይም። በአገር ውስጥ ከሚካሄደው ጦርነት በተጨማሪ የአገሪቱ ሉዓላዊ ድንበር ተድፍሮ፣ የውጭ ዜጎች እንደልባቸው እየገቡ ዜጎቻችንን የሚያፈናቅሉበትና ሃብቷን የሚዘርፉባት አገር ሆናለች አገራችን። ኢትዮጵያ በዙሪያዋ ከሚገኙ ጎረቤቶቿ ጋር ሰላም የሌላት በመሆኑም የዓለም አቀፍ ግንኙነቷም ከፉኛ ተጎድቷል።

በፖለቲካው ረገድም ቢሆን የተሻለ ነገር የለም። ጋዜጠኞች ሞያዊ ግዴታቸው በሚጠይቀው መሠረት የአገራችንን ነባራዊ ሁኔታ በመከታተል በሃቅ መዘገብ ያስደብድባል፣ ያሳፍናል፣ ያሳስራልም። ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ ብቻ በርካታ ጋዜጠኞች ታስረዋል። በሰላማዊ መንገድ የሚታገሉ የድርጅት መሪዎችና አባሎች፣ ታፍነዋል፣ ታስረዋል፣ ተገለዋል። አንዳንዶቹም ደብዛቸው ጠፍቷል።

ኢሕአፓ በስምንተኛ ጉባዔው ላይ በወሰነው የሰላማዊ ትግል አቅጣጫ መሠረት በአገሪቱ ውስጥ ሰላማዊ ትግሉን በማራመድ በፖለቲካው፣ በኤኮኖሚውና በማኅበራዊ ዘርፍ ዕኩልነት፣ ማኅበራዊ ፍትኅና ዴሞክራሲ እንደሰፍን ለማድረግ በሰላማዊና ሕጋዊ መንገድ እየታገለ የሚገኝ ድርጅት ነው። ኢሕአፓ በአገራችን ውስጥ የተንሰራፋውን የተዛባ ማኅበራዊ፣ ኤኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ ሥርዓት በመታገል ለአገር መረጋጋት፣ ሰላምና ዕድገት ይበጃሉ የሚላቸውን የፖሊሲ አቅጣጫዎች በመንደፍ፣ አማራጭ ራዕዩን ለሕዝብ ለማሳወቅ ከፍተኛ ጥረት አድርጓል። የሰላማዊ ትግሉ የድርጅቱን አባላት፣ አመራሮቻችንንና ደጋፊዎችን በብዙ መልኩ ዋጋ እያስከፈል ይገኛል። ይህ ሁሉ የሚደረገው ለሕዝባችንና ለአገራችን ድርጅታችን ያለውን ራዕይ በይፋ በማቅረቡና የገዢውን ፓርቲ የተሳሳቱ ፖሊሲዎችና እርምጃዎችንም ለሕዝብ በግልጽ በማቅረቡ ነው።

የኢሕአፓን ሰላማዊ ትግል የማፈን እርምጃ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እጅግ ተጠናክሮ ቀጥሏል። ለምሳሌ የድርጅታችን ሊቀ መንበርና ተቀዳሚ ምክትል ሊቀመንበር "ጦርነት ይቁም ሰላም ይስፈን" በማለት ከሌሎች ድርጅቶች አባላት ጋር ሰላማዊ ሰልፍ እንዲካሄድ ለማስተባበር ጥረት በማድረጋቸው እንቅስቃሴያቸው እንደ ወንጀል ተቆጥሮ ከአዲስ አባባ እስከ አዋሽ አርባ በሚገኙ እስር እሥር ቤቶች ውስጥ ታስረው ለወራት እንዲሰቃዩ ተደርጓል። በቤኒሻንጉል ጉምዝ የሚገኙ የድርጅታችን ተጠሪም በተመሳሳይ ሁኔታ ለእስር ተድርገዋል። አሁንም በተለያየ መልክ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ በድርጅታችን መሪዎችና አባላት ላይ ከድርጅቱ እንዲለቁ ከፍተኛ ማስፈራራትና ተጽዕኖ እየተደረገባቸው ይገኛል። ከዚህም ሌላ ጠ/ሚኒስቴር አብይ

በተደጋጋሚ በተካሄዱ ስብሰባዎች ላይ ከአንድ የአገር መሪ በማይጠበቅ ደረጃ በኢሕአፓ ላይ እጅግ አፀያፊ የስድብ ናዳ ሲያወርዱበት በይፋ ተደምጠዋል።

ይህ ሁሉ የሚሆነው ኢሕአፓን በማሸማቀቅ በተሳሳቱ የመንግሥት ፖለሲዎች ላይ ያለውን ተቃውሞ እንዳያሰማ፣ ለሕዝብና ለአገር ያለውን የዕድገት፣ የነፃነትና የሰላም ራዕይ እንዳያቀርብ፣ ከተቻለም ከሰላማዊ የትግል መስመሩ ለማስወጣት ሆን ተብሎ እየተካሄደ ያለ እኩይ ተግባር ሆኖ አግኝተነዋል። ይህ ድርጊት መሠረታዊ የድርጅት መብትን የሚፃረር ብቻ ሳይሆን በአገር ውስጥ ሰላምና መረጋጋት እንዳይሰፍንና ለፖለቲካ ብዙሃዊነትን የማያግዝም ሆኖ አኝተነዋል።

በመሆኑም ይህ የድርጅቶችን ሕልውና የሚገታ እርምጃ በስቸኳይ እንዲቆም እያሳሰብን ድርጊቱ ኢሕአፓን ብቻ ሳይሆን በሌሎች የፖለቲካ ድርጅቶች ላይ የሚያስከትለውን ከፍተኛ አደጋ በመገንዘብ መንግሥት ከዚህ ተግባሩ እንዲታቀብ ሃቀኛ የፖለቲካ ድርጅቶች ሁሉ አስፈላጊውን ግፊት እንዲያያደርጉ ጥሪያችንን እናቀርባለን።

እኛ ከኢትዮጵያ ውጭ የምነገኝ የኢሕአፓ ደጋፊዎች በድርጅቱ አባላትና ደጋፊዎች ላይ የሚደረገውን ተጽዕኖና ወከባ እያወገዝን የኢትዮጵያን ሕዝብ ነፃነት፣ እኩልነትና አንድነት እውን ለማደረግ በሚደረገው ትግል ውስጥ ዛሬም እንደ ትላንቱ ትግላችንን አጠናክረን እንደምንቀጥል ለሕዝባችንና ለፓርቲያችን ቃል እንገባለን።

አንድነቷ ተጠብቆ እኩልነትና ነፃነት ለሚሰፍንባት ኢትዮጵያ በጽናት እንታገላለን!

ነሃሴ ፲ ቀን ፪ ሺህ ፲፯ ዓ. ም

August 16, 2024